# መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ -መኢሶን-

# ALL ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE)

"NEW ETHIOPIA" P.O.BOX 5077 18305 SPANGA SWEDEN


ግንቦት 16፣ 1982

## "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል"

የግንቦት 1981 የሠራዊቱ እንቅስቃሴ ካለፈ ከአንድ አመት በኋላ ግንቦት 12 ቀን 1982፣ መንግስቱ ሃ/ማርያም 12 ጀኔራሎችን በሞት 2 ጀኔራሎችን በዕድሜ ልክ እስራት ቀጥቷል። የተገደሉት ጀኔራሎች ኃይሉ ገ/ሚካኤል፣ ወርቁ ዘውዱ፣ አለማየሁ ደስታ፣ ዘውዱ ገብረየስ፣ ሰለሞን በጋሻው፣ ደሰልኝ አበበ፣ ተስፋዬ ደስታ፣ እንግዳ ወ/አምላክ፣ እርቅ ይሁን በደሰ፣ ነጋሽ ወልደየስ፣ ገናናው መንግስቱና ተስፋዬ ትርፌ ሲሆኑ እድሜ ልክ የተፈረደባቸው ደግሞ ሪር አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኑና ጀኔራል አብዱለሂ ኡመር ናቸው።

እንደሚታወሰው ሁሉ የግንቦቱ የሠራዊቱ እንቅስቃሴ በየግንባሩ ያለው ጦርነት ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈታ፣ ተቃዋሚ ኃይሎችን ያቀፈ የጋራ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም፣ የህዝቡ የመናገርና ሃሣብን የመግለጥ መብት እንዲከበር፣.... የሚሉ መፈክሮችን ይዞ የተነሳ ንቅናቄ ነበር። የዘሬ አመት ንቅናቄው ሲከሽፍ የተገደሉት ጀኔራሎች መርዕድ ንጉሤ፣ ደምሴ ቡልቶ፣ አምሃ ደስታ ... እና ሌሎችም እንዲሁም አሁን የሞት ቅጣትና እድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው ጀኔራሎች ይህን የሠራዊቱን ጥያቄ የመሩና የደገፉ መሆናቸው ይታወቃል። መንግስቱ ሃ/ማርያም በተለመደው ከሳሽና ሀሰተኛ አንደበቱ ንቅናቄው «የጥቂት ስልጣን ጥመኛ ጀኔራሎች» ሴራ ብሎ ሊያልፈው ሞክሮዋል። በአገሪቱና በየጦር ግንባሩ የነበረውን ውድቀት በነዚህ ሰዎች ላይ አለከ ለማለፍም የተቻለውን ሁሉ ማድረጉን በ«<u>ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ</u>» ጋዜጣችን መጥቀሳችን ይታወሰል። በየአደባባዩ «ጥቂት» እያለ ቢዘበንንም ከ250-300 የሚገመቱ መኮንኖችን እንዳሰረና እንደገደለም የአደባባይ ምስጢር ነው። ከዘሬው የአብደት እርምጃው በፊትም፣ እነ ጀኔራል ፋንታ በላይ፣ ተከልኝ ንጉሤና ውበቱ ፀጋዬን የመሰሰሉ የንቅናቄውን መሪዎችና ተሳታፊዎች ለፍርድ እንኳን ሳይቀርቡ አሰቃቂ በሆነ መንገድ ከሰቃየ በኋላ አስገድሏቸዋል። ሌሎች ቁጥራቸው የበዛ የንቅናቄውን ደጋፊዎችም እንዳሰረና እንደገደለ ይታወቃል።እነዚህ የሞትና የእስራት ቅጣት የተፈፀመባቸው ጀኔራሎችም ፍርዳቸው በይፋ ለህዝብ ክፍት ሆኖ እንደሚታይ ከተነገረ በኋላ በዝግ ችሎት እንደተወሰነባቸውና ዳኞቹም (እነጀኔራል ተስፋየ ገብረ ኪዳን) ሙከራውን ያከሸፉ የመንግስቱ ታማኝ አሽከሮች፣ ፍ/ቤቱም የይስሙላ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

መንግስቱ ሃ/ማርያም ከግንቦቱ የሠራዊቱ እንቅስቃሴ በኋላ አንዳንድ መጠነኛ ለውጦች ለማድረግ ቢሩዋሩዋጥና የከቲት 26፣1982 ዓ.ም. ባደረገው ንግግር ለተቃዋሚ ኃይሎች ሀልውና እንደሚሰጥ ለዘብ ያሉ የኤኮኖሚ ለውጦች እንደሚያደርግና የርዕዮተ አለም አክራሪነቱን እንደሚያቆም ቢምል ቢገዘትም ይህ አሰቃቂ ፍርድ የተከሄደው እነዚህ ቃለት በተነገሩ በስት ወራት ውስጥ መታወስ ይኖርበታል።የአገር ውስጥ ትግል ማየል፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታዎች መተረማመስ እንዲሁም አለም አቀፍ ሁኔታው መንግሥቱን ብዙ እንዲቀባጥር አስገደዱት እንጂ መሠረታዊ ባህርዩን እንዲለወጥ አላደረጉትም። የከቲት 27 ቀን 1982፣ መኢሶን በወጣው ልዩ መግለጫ እንደተጠቀሰው «ሰለምና ዲሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም

የፓርቲውን ስም ቀየረ አልቀየረ፣ ኢኮኖሚውን ቀየጠ አልቀየጠ አገሪቱ ከምትገኝበት የፖለቲካ ጭቆና፣ የኢኮኖሚ ውድቀትና የጦርነት አዘቅት ልትላቀቅ አትችልም»።

የመላ ኢትዮጵያ ሶሺሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ይህን የመንግሥቱን አረመኔያዊ እርምጃ አጥብቆ ያወግዛል። እንደዚህ አይነቱ ፋሽስታዊ እርምጃ መንግሥቱ ግብአተ መሬቱ መቅረቡን አወቆ፣ «መጥፋቴ ካልቀረ አጥፍቼ ልጥፋ» ብሎ መነሳቱን ያሰያል ብሎ ያምናል። «ትንኝ እንኳን መግደል» ያስቀቀኛል የሚለው መንግሥቱ፣ «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» በሚል ገና ብዙ የኢትዮጵያን አገር ወዳድ ልጆች እንደሚጨፈጭፍና አገራችንንም ወደከፋ ጉዳና እንደሚጉትታት በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

ሰላምና ዲሞክራሲ የሰፈነበት አዲሲቱ ኢትዮጵያ የምተመሰረተው፣ ለችግራችን ሁሉ መንስኤ ከሆነው ከመንግሥቱ አገዛዝ በሽገር መሆኑን መኢሶን አይጠራጠርም። የመንግሥቱ አገዛዝ ሳይወድቅ በአገራችን ዲሞክራሲና ሰላም ይሰፍናል ማለት ወይም የተቃና ሽግግር ይደረጋል ማለት ከቶም የማይታሰብ ነው። ይልቁንስ፣ ለሰላምና ለዲሞክራሲ የቆሙ ኃይሎች ሁሉ ልዩነቶቻቸውን አቻችለው የመንግሥቱን አገዛዝ ማውደምና በምትኩም <u>የጋራ የሽግግር መንግሥት</u> ማቆም የጊዜው ቀዳሚና አጣዳፊ ጥያቄ መሆኑን አስተውለው ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ በቅን መንፈስ እንዲነሱ መኢሶን ጥሪውን ያድርሳል።

<u>መኢሶን</u>